# የዘንድሮው (1997 ዓ.ም.) ምርጫ
# የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶችና የወያኔ ሩጫ

በሎስ አንጀለስ
የኢትዮጵያ ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሕብረት (ኢዴኃሕ)
የድጋፍ ኮሚቴ

**የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥንትም ዛሬም ከሽብርተኛ አምባገነን መንግሥቶች ጋር የሚያካሂደው የሰላምና የአመጽ ትግል**

የዛሬውን ከትናንቱ ጋር ለማስተሳሰር የታሪክ አቡነ ዘበሰማያትን የግድ ይላል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ራሱ ባፀደቀው ሕገ መንግሥት መሠረት የሚፈልገውን አስተዳደርና ስርዓት የመምረጥ መብት ኖሮት አያውቅም።

ከጥንት እስከ ዛሬ ያፀደቀው ሕገ መንግሥትም ሆነ የመረጠው መንግሥት በታሪኩ ውስጥ ተፈልጐ አይገኝም። ዛሬም እየተገዛ ያለው በዚያው በጥንቱ በአምባገነንነት ስርዓት ነው። በአምባገነኖች መንግሥት ነው።

እስከ ደርግ ዘመነ መንግሥት ድረስ ኢትዮጵያ ላይ ለዘመናት ተንሰራፍቶ የቆየው የጉልተኝነት ሥርዓት (feudalism) እንደነበር ሁሉም የሚያውቀው ነው። የዚያ ስርዓት መሪዎችና ተጠሪዎች በጉልበት ያገኙት ስልጣን ከፈጣሪ የተሰጠና የተፈቀደ ተደርጐና ተመስሎ ይነገር /ይሰበክ ነበር። የስልጣናቸው ምንጭ መለኮታዊ እና ሰማያዊ እንጂ ሕዝባዊ እና ምድራዊ አልነበረም ማለት ነው። በመሆኑም አስተዳደራቸው በሕዝብ ይሁንታና መብት የሚገታበትና የሚለጐምበት ምክንያት አልነበረውም።

ሕጋቸውን፣ ዳኝነታቸውን (ስርዓታቸውንና አስተዳደራቸውን) መቋቋምና መቃወም ፈጣሪን ከመጋፋትና ከመዳፈር የሚያስቆጥር ሆኖና ተደርጐ ይተረጉም ነበርና። የፈጣሪ ምድራዊ ተወካዮችና ተጠሪዎች ሆነውና ተደርገው ይታዩ ነበርና!

“ንጉስ አይከሰስ ሰማይ አይታረስ” ተብሎ የሚተረተው የዚያ ስርዓት ቁንጮ መሪዎች ስልጣን ምሉዕ በኩለሄ (absolute) የነበረ መሆኑን ለመግለጽና ለማመልከት ያህል ነው። በዚያው ልክ ደግሞ ሰፊው ሕዝብ የኔ ነው የሚለው አንዳችም መብት አልነበረውም። በሕዝቡም በምድሩም ላይ የሚያዝዙበት ንጉሦችና ስርዓታቸው ብቻ ስለነበሩ/ ስለነበረ። “ሁሉም የንጉስ (ንጉስ=መንግሥት) ባርያ ነው” የሚለው አነጋገር የንጉሦችን ባለ-ሁሉ መብትነት / የሕዝብን መብት-የለሽነት ቁልጭ አድርጐ የሚያስታውሰን ነው።

እስከ የካቲት 66 ዓ.ም. ድረስ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጉልተኝነትን ነቃቅሎ በዴሞክራሲያዊና ሕዝባዊ ስርዓት ለመተካት ተደራጅቶ ለመነሳት ዝግጅትና ብቃት አልነበረውም።

## *የኢትዮጵያ ሕዝብ የፖለቲካ መብት ባለቤትነት እና የዴሞክራሲ ጥያቄ*

እጅግ በተጠቃለለ አነጋገር፣ የሕዝብ የፖለቲካ መብት ባለቤትነትና የዴሞክራሲያዊ መንግሥት ጥያቄ በቅድሚያ የተነሳውና የተመለሰው በምዕራብ አውሮፓ አገሮች እንደሆነ የሚታወቅ ነው።

በመሬት ባለቤትነት ላይ ተመስርቶ በቀጣይነትና በተከታታይነት ለዘመናት ተንሰራፍቶ የቆየው የጉልተኝነት (feudalism) ስርዓት በኢንዱስትሪ እድገትና ባለቤትነት ላይ በተመሰረተው ስርዓት (capitalism) ከተሸነፈና ከተተካ በኃላ ነው።

በጉልተኝነትና በአዲሱ የከበርቴ ሥርዓት መካከል የተካሄደው ትግል ውጤት ነው።

- ሕዝብ የፖለቲካ መብት ባለቤት መሆኑን፣
- ሕዝብ የፈለገውን መንግሥት በድምጽ ብልጫ (አንድ ሰው/ አንድ ድምጽ) ስልጣን ላይ የማውጣት/ የማይፈልገውን ከስልጣን የማውረድ መብቱ ተረጋገጠ።
- የመንግሥት ተጠሪነትና ተወካይነት ለሕዝብ እንጂ ለሌላ ምድራዊ ሆነ መለኮታዊ ኃይል ስላይደለ የመንግሥትና የሃይማኖት ተቋሞች ሚና ተለዩ። ምድራዊውና ሰማያዊው ተለያየ።
- የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎች በነፃ ተደራጅተው ለመንግሥት ስልጣን የመወዳደር መብታቸው ታወቀ / ተጠበቀ።
- የሕዝብ የማይገረሰሱና የማይጣሱ (inviolable) መሠረታዊ የዜግነትና የሰብአዊ መብቶች፣ ሕገ መንግሥታዊ መብቶች (constitutional rights) ሆነው ተከሰቱ።

በአጭሩ የዴሞክራሲያዊ መንግሥትና የመድብለ ፓርቲ ስርዓት በምዕራብ አውሮፓ አገሮችና በኃላም በዩናይትድ እስቴትስና በካናዳ ስር እየሰደዱና እየዳበሩ መጡ።

## *የመብት ትግል ሽግግር / ከመብት ልመና ወደ ሕዝባዊ አመጽ*

ከአውሮፓ አገሮች የኢንዱስትሪ እድገት ጋር ተያይዞ የተስፋፋው ዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም እና ያስከተለው የሁለተኛ ዓለም ጦርነትና ውጤት የኋላ ቀርና የቅኝ ተገዡ ሕዝቦችን የነፃነት እንቅስቃሴና ትግል ወለደ።

ኢትዮጵያም "ለሺህ ዓመታት ዓለምን ረስታ፣ እርሷም በዓለም ተረስታ"፣ ቤትዋን ዘግታ ከተኛችበት በርዋ ሲንኳኳ በርግጋና ደንግጣ ተነሳች። ሕዝብን ባርያ አድርጎ መግዛት፣ የገዢዎች መለኮታዊ መብት እንዳልሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመገንዘብ ቻለ። የፖለቲካ መብት ባለቤት የአንድ አገር ሁለንተናዊ መሠረት ሕዝብ መሆኑን ተረዳ። አመነ፣ ተቀበለ። ካለፈቃዱና ካለፍላጎቱ በጉልበትና በፈጣሪ ስም እንደ ፈረስ የሚጋልቡትን እንዳጋሰስ የሚጭኑትን ነፍሰ በላዎች የሚገላገልበት ጊዜ እንደተቃረበ ተሰማው። በተማሪዎች የመሬት ለአራሹ ጩኸት፣ የሕዝባዊ ዘመን መለወጫ ደወል ተደወለ። የደወሉ ድምጽ ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጆሮ ገባ። ከዳር እስከ ዳር ተሰማ። የዘመናት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕልም ተፈታ። እውን ገሃድ ሆነ። ሕዝባዊ ፍትሐዊ እሳተ ገሞራ በአሮጌው ስርዓት ላይ ፈነዳ። ታሪካዊው የ66ቱ የካቲት

የአዲስ

አብዮታዊ አመጽ ታሞጦ ተወለደ። ሽብር ሆነ። በአመጽ እያሸበሩ ይገዙ የነበሩ የስርዓቱ መሪዎች ተጠቃሚዎችና ተቆርቋሪዎች ተራ ደርሷቸው (ተራ ደርሶባቸው) በሕዝባዊ አመጽ ተሸበሩ። <u>አሸባሪዎች ተሸበሩ</u>!

ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጊዜ አግኝቶ ተወያይቶ የራሱን ሕገ መንግሥት አጽድቆ ለእርሱ የቆመ ስርዓትና መንግሥት የመመስረት መብቱ ገና ሳይድህና ጠንቶ ሳይቆም በጅምርና በውጥን ላይ እንዳለ ተጨናግፎ ተቋረጠ። በአጭር ተቀጨ።

የፖለቲካ መብት ባለቤትነቱ በታጠቀ አሸባሪ ቡድን ተነጠቀ። ከየክፍለ ጦሩ ተለቃቅሞና ተጠራቅሞ ውሎ አድሮ ራሱን ደርግ ያሰኘው የወታደሮች ቡድን በጉልበትና በጠብመንጃ ኃይል የመንግሥት ስልጣን ያዘ። የራሱን የሽብርና የአፈና መዋቅር ከዘረጋ በኋላ ራሱን በራሱ መርጦ "ሕዝባዊ" መንግሥት ነኝ አለ። ፓርቲም መንግሥትም ሆነ።

"ጥሮ ግሮ ባመጣው ነጋዴ፣ ኩበትን ጋሻ አርጎ ነጠቀው ወንበዴ" እንዲሉ፣ የሕዝብና የወገኖቹ ትግልና ውጤት በጉልበትና በጠመንጃ ኃይል ተነጠቀ። ከንብ ቀፎ ዝንቦች ገቡ። ማሩን አሟጥጠው ባዶውን ቀፎ ጥለውት ሊሄዱ። ወታደርነቱን (ጠብመንጃ ነካሽነቱን)፣ የሰለጠነበትን የመግደልና የመጨፍጨፍ ሙያውንና ሚናውን ተራማጅና ሕዝባዊ ለማስመሰል፣ ከስርዓት ልብሳቸው ላይ (ዩኑፎርማቸው ላይ) "ሶሻሊዝም"" የሚል የክርስትና ስም ለጠፉ። "የመልከ ጥፉ በስም ይደግፉ" እንዲሉ። "የወታደሮች ሶሻሊዝም"/ "የጦር ሰፈር ሶሻሊዝም" ('garrison socialism") በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ታወጀ። በአዋጅና በግዳጅ የሰፌው ሕዝብ መንግሥት ስለተደረገ፣ የሽብርተኛውን ወታደራዊ ስርዓትና ፖሊሲ የመረመረና የጠየቀ ሁሉ ከፀረ ሕዝብ ተፈርጆ ተፈጀ። በአብዮትና በሶሻሊዝም ስም ሁልቆ መሳፍርት የሌለው ሰው እየታጨደ እንደ ቆሻሻ ከወል ጉድጓድ (mass grave) ውስጥ ተራግፎ ተጣለ። ሌላ ሌላም እጅግ ዘግናኝ የሆኑ፣ ተቆጥረው ተዘክረው የማያልቁ ድርጊቶች በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ተፈጸሙ።

ሬሳ ለመውሰድ የጥይት ዋጋ ተከፈለ። እናት አባት ስለተረሸኑ ልጆቻቸው ሙሾ በማውረድ ፈንታ፣ "አበጀሽ አብዮቴ" እያሉ እስክስታ እንዲወርዱ ተገደዱ። በሕዝብ ስም፣ ሕዝብ ተመነጠረ። በ"ፍየል ወጠጤ" ዜማ እየተቀደሰ። የደርግ ፋሽስታዊ ተግባር፣ የካቲት 12ትን የልጆች ጨዋታ አስደረገው። የአገር ሰው በአገር ሰው ላይ የፈጸመው ግፍና በደል ባእድና ኢትዮጵያዊ የሚለውን ልዩነት ፈጽሞ አጠፋው። ትርጉምና ፍች የሌለው አደረገው። የአገር መውደድና የጀግንነት ስሜት በአገር ጥላቻና በፍራቻ ተተካ።

የደርግን መንግሥታዊ ሽብርተኛነት ያላየ ወይም ያልሰማ ስለማይኖር ረጅም ማብራሪያና ማስረጃ የሚጠይቅ አይደለም። ለአስራ ሰባት ዓመት ኢትዮጵያን አድቅቆ ራሱም ደቀቀ። ወደቀ። አሁንም እንደቀድሞው የተደራጀና የተጠናከረ ዴሞክራሲያዊ ኃይል ስላልነበረ የመንግሥት ስልጣን በሌሎች በታጠጠቁ ሽብርተኛና ፋሽስታዊ ኃይሎች እጅ ወደቀ። <u>ለአገር አንድነትና ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት የሚታገሉትን የኢትዮጵያ ፖለቲካ ድርጅቶች ሆን ብለው ባገለሉ የባዕዳን ኃይሎችና መንግሥቶች እየተረዱና እየተመሩ</u> ሻዕቢያና ወያኔ ኢትዮጵያን ተቆጣጠሩ። በሻዕቢያ የበላይነት ለሰባት ዓመት ተጣምረውና ተባብረው የኢትዮጵያን ንብረትና ሀብት ተከፋፈሉ።

የደርግን የመንግሥት፣ የመከላከያና የኤኮኖሚ መዋቅር ሁሉ አፈራረሰ። የሰሩትና ያደረጉት ሁሉ ፀሐይ የሞቀው፣ አገር ያወቀው ነው። ታይቷል፣ ተነግሯል፣ በዝርዝር ተጽፎ ተነቧል። ስለሆነም ያንኑ እዚህ ላይ መድገም አስፈላጊም ጠቃሚም አይሆንም።

በፀረ ደርግነትና በአፍቃሪ ዴሞክራሲነት ስምና ሽፋን፣ ወያኔ በሕዝብ ስም ራሱ ያፀደቀውን ሕገ መንግሥት ደነገገ። የአንድ ፓርቲና የአንድ መንግሥት መዋቅር ዘረጋ። መንግሥትም ፓርቲም ሆነ። ልክ እንደ ደርግ።

ሕብረ ብሔራዊ ለመምሰል፣ በተፈለገ ጊዜ የሚተከሉና የሚነቀሉ የሚበዙና የሚቀነሱ፣ በራሳቸው መቆምና መንቀሳቀስ የማይችሉ ሽባና ተለጣፊ የብሔረሰብ ድርጅቶችን ጠፍጥፎና ቀፍቅፎ ፈጠረ። በሸነሸነው ክልል ሁሉ ዘርቶ አሰራጨ። በብሔረሰቦች እኩልነትና ነፃነት ስም በካድሬዎቹና በተለጣፊዎቹ ድልድይነት፣ ታዛዥነትና ተላላኪነት የመላውን ሕዝብ (የመላውን አገር) መብትና ንብረት ብቸኛ ባለቤት ሆነ።

የዴሞክራሲና የመብት ጥያቄ ያነሳውን ሁሉ አስፈራራ፣ አሰረ፣ አሳደደ፣ ገደለ። የመኖሪያ፣ የመላወሻና የሰርቶ ማደሪያ በሮችን ሁሉ ጠርቅሞና ደርግሞ ዘጋ። የወያኔ አቃፊና ደጋፊ ባልሆነው ላይ ሁሉ።

አምባገነንነቱና አሸባሪነቱ አሁንም እንደቀጠለ፣ እንደተቀጣጠለና እንደተባባሰ ነው። አምባገነንነቱና አሸባሪነቱ እንደ ደርግ ሆኖ በስልቱና በድርጊቱ ግን እጅግ የሰላና የረቀቀ ነው። የደርግ የፊት ለፊት፣ የጠራራ ፀሐይ፣ ያውላላ ሜዳ ግድያና ጭፍጨፋ በወያኔ ዓይን ሲታይ፣ "ማሞ ቂሎ"ን የሚያስተርትበት ነው!

ደርግም ወያኔም ሽብርተኛ መንግሥቶች (terrorist states) ናቸው። ወያኔን ከደርግ ልዩ የሚያደርገው በአንድ ብሔረሰብ የበላይነትና ተጠቃሚነት ላይ ብቻ ያተኮረ (ethnocentric/terrorist state) መሆኑ ነው። በትግራይ የበላይነትና ተጠቃሚነት ላይ ብቻ ያተኰረ እና የተዋቀረ ሽብርተኛ መንግሥት መሆኑ ነው። በመሆኑም ሽብርተኛነቱ፣ የክልልተኛነትና የጐጠኝነት ባሕርይም የተዋሃደው ነው። ከፋፍሎ ለመግዛት የሚከተለው ፖሊሲ፣ የተለያዩ ብሔረሰቦችንና ክልሎችን በየጊዜው የማጋጨትና የማሸበር ተግባሩና ስልቱ ከማንም የተሰወረ አለመሆኑ ነው።

የደርግ አሸባሪነት ግን ብሔረሰብ ዘለልና አገር አቀፍ ባሕርይ (ሁሉ አዳራሽ) ነበረው። የተቃወመው ሁሉ ጠላቱ/ የቀረበውና የታዘዘው ሁሉ ወዳጁ ነበር። አሸባሪነቱ አገር አቀፋዊነት ብቻ ሳይሆን "ዓለም አቀፋዊነት" (internationalist) ባሕርይ የነበረው ነው! "<u>ሶሻሊስትነቱ</u>" በትክክል ተግባር ላይ የዋለው <u>በሁሉ አሸባሪነት</u> ባሕርይ ነው። ሁሉን ጨርግዴ፣ በብሔር በሃይማኖት፣ በፆታ/በእድሜ የማያዳላና የማይመርጥ አንድ አድርጐ ገዳይ (equal opportunity killer) የነበረ በመሆኑ ነው።

ወያኔ ግን በእጅ አዙር፣ በጭለማ፣ በስውር ይገድላል። አስፈላጊ ሲሆን ገድሎ ለቅሶ ይደርሳል! እስር ቤት ያበሰብሳል። ሕጋዊ አስመስሎ የሰዎችን ንብረት ይወርሳል። የወያኔ ተንኮልና አሸባሪነት ለብዙሃኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ የዕለት ስንቁ መዋያ ማደሪያው ነው። ለቀባሪ እንደ ማርዳት ነው። በራሱ በትግራይ ሕዝብ ሐውዜን ላይ የፈጸመውን (ያስፈጸመውን) ብቻ ጠቅሶ ማለፍና ማስታወስ በቂ ነው።

## በሕዝብ ያልተመረጡ መንግሥቶች ሽብርተኛ መባላቸውና መሰኘታቸው ትክክለኛ አጠራር የሚሆነው ለምንድር ነው?!

የሕዝብን የፖለቲካ መብት ባለቤትነት ረግጠው የቡድናቸውን ጥቅም ለማስከበር በሕዝብ ስም በሕዝብ ላይ በአመጽ የተደገፈ ስርዓት ስለሚያስፍኑ ነው። ስለሆነም፣ ሕዝብ አማራጭ አጥቶ መብቱን ለማስከበር በአመጸ ቁጥር፣ አምባገነን መንግሥቶች በአሸባሪነት ይፈርጁታል። እነርሱ በሕዝብ ላይ የሚፈጽሙት አመጽ ግን አሸባሪነት መሆኑ ቀርቶ የሕግና የስርዓት አስከባሪነት ሚናና ባሕርይ ያላብሱታል። ለመብቱ ሲታገል የሚያስሩትን፣ የሚያሳድዱትን የሚረሽኑትንና የሚጨፈጭፉትን ሁሉ "ቦዘኔ፣ ዘራፊ፣ ወንበዴ፣ ስርዓት አልበኛ..." ይሉታል። ያስብለታልም።

የሚከበረውና የሚጠበቀው የማን ስርዓትና ሕግ ነው? የአምባገነኖች ስርዓትና ሕግ ወይስ ሕዝብ የደነገገው ስርዓትና ሕግ? የአሸባሪና የተሸባሪ ማንነት ተለይቶና ተለክቶ የሚታወቀው በማንና በየትኛው መስፈርት ነው? አምባገነኖች፣ የሕዝብን መብት፣ ጥቅምና ንብረት የሚቀሙትና የሚዘርፉት፣ የማስገደጃና የማፈኛ ኃይሎችንና መዋቅሮችን (በአገርና በሕዝብ ስም የተቋቋሙትን የጦር፣ የፖሊስ፣ የስለላ... ተቋሞችን) በመቆጣጠርና በመጠቀም ነው። እንጂ በተቻለውና ባመቸው መንገድና ስልት የሚገባውን መብት ለማስመለስ አምፆ ከመነሳት የተለየ አማራጭ የሌለው ሕዝብ ሊሆን አይችልም። የመንግሥት ስልጣን ከሕዝብ በአመጽ (በጉልበት) ነጥቀው፣ ሕዝብን በአመጽ የመግዛት ብቸኛና ዘላለማዊ ባለመብቶች አምባገነኖች ናቸው ካልተባለ በስተቀር! ሕዝብ ሁልጊዜም የመገዛት እንጂ ምንጊዜም ራሱን የመግዛት (በመረጠው መንግሥትና ስርዓት የመተዳደር) መብት የለውም ማለታቸው (አምባገነኖች) ካልሆነ በስተቀር! ታዲያ ከዚህ ሌላ ምን ማለት ሊሆን ይችላል?!

የሕዝብ አመጽ ለመብትና ለነፃነት ሲሆን የአምባገነን መንግሥቶች አመጽ ግን መብትንና ነፃነትን ለማፈን ነው።

የነዚህ ዓይነት መንግሥቶች ተልዕኮ ግልጥና የማያሻማ ነው። መብት አልባ ሆነህ ተገዛ ነው። የሕዝብ መልስ (አመጽ) ደግሞ መብቴን አልሰጥም/ እንቢ አልገዛም ነው።

በአፄ ኃይለ ስላሴ ዘመነ መንግሥት፣ የጐጃም፣ የባሌ፣ የጌዴኦ... ሕዝብ በአቤቱታ፣ ለንጉሡ ነገስቱና ለሹሞቻቸው በደሉን፣ ብሶቱንና ፍላጐቱን ደግሞ ደጋግሞ ካሰማ በኋላ ነው። በስርዓቱ ላይ እጁን ያነሳው/ በአመጽ የተነሳው። እንጂ በቤቱ፣ በመንደሩ እና በቀዬው ላይ የወረደው የቦንብና የመትረየስ ናዳ ናፍቆትና ጠምቶት አልነበረም።

በአጭሩ ለመብት መታገልና ማመጽ የትኛውም ሕዝብ የአልሞት ባይ ተጋዳይነት መብት ነው። ለዘላለም ለመንጠቅም ለመከልከልም፣ የማይቻል መሠረታዊ የሰው ልጅ መብት ነው።

በአምባገነን መንግሥቶች አመጽና በሕዝባዊ አመጽ መካከል ያለው ልዩነት፣ አንደኛው ባርነትን ለማሰንበት ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ባርነትን ለማስወገድ ነው። በባርነት ወይም በነፃነት የመኖር ምርጫና ትግል ነው።

ታዲያ በወያኔ/ኢህአዴግ ላይ የሚነሳ የሕዝብ አመጽ ሽብርተኛነቱ ከምን ላይ ነው? አሸባሪውና ተሸባሪውስ ማን ሊሆን ማን ሊባል ነው??

## የዘንድሮው ምርጫ የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶችና የወያኔ ሩጫ

ወያኔ ባላገሩንም ከተማውንም አስፈራርቶና አስገድዶ ራሱን በራሱ ሁለት ጊዜ መርጦ ተመረጥሁ ማለቱን የማያስታውስ የለም። የራሱን ርምጫ የሕዝብ ምርጫ አስመስሎ የዴሞክራሲያዊነቱና የተወዳጅነቱ ማስረጃና ማስተማመኛ አድርጎ ለማሳየት ባከነ። ስልጣን ላይ ካስወጡት መንግሥቶች የሚቸረውን ድጋፍና ሁለንተናዊ እርዳታ እንዳይቀነስበት/ እንዳይቋረጥበት።

በአስገዳጅነትና በተቆጣጣሪነት ራሱን በራሱ በማስመረጥ ልማድ ተማምኖ፣ አሸናፊነቱን ለሦስተኛ ጊዜ ለማስመስከር ወሰነ። በጡጫም በሩጫም የሚችለኝ የለም የሚለው ወያኔ፣ ሁሉንም ተቃዋሚ ድርጅቶች በሰላማዊና በሕጋዊ መንገድ ሮጠው እንዲወዳደሩት ጥሪ አቀረበ።

በሕጋዊና በሰላማዊ መንገድ የምትፈልገውንና የምትፈቅደውን መንግሥትና ስርዓት የመምረጥ መብትህ ይከበራል/ ይጠበቃል ተብሎ ተነገረው። ለኢትዮጵያ ሕዝብ።

ፍትህ ጠፋ / በደል በዛ ብለህ ብረት አንስተህ፣ ዱር ቤቴ ብለህ ለአመጽ አትገፋፋ ተባለ። ደም ሳታፈስ/ መንግሥት ሳታፈርስ የፖለቲካ መብት ባለቤትነትህን በምርጫ ሳጥን ታስረግጣለህ፣ ከቀዬህ ሳትርቅ፣ ከቤትህ ሳትወጣና ስራ ሳትፈታ ምርጫህን ታገኛለህ አሉት።

ስለሆነም አመጽን እንደአንድ የትግል ስልት ከሚቆጥር አመጽን ላንዴም ለሁሌም ከማያወግዙ (ብታሰር/ ብገረፍ፣ ብገደል/ ብሰቀል ወያኔ ፍርድ ቤት ከመሄድ ውጪ አላስብም/ አላሳስብም ብሎ ከማይፈርም) የፖለቲካ ቡድን ሁሉ፣ ውጉዝ ከመአርዮስ ብለህ መራቅ ግዴታህ ነው ብለው በምክር መስል ትዕዛዝ አስጠነቀቁት። ሙያሌ ማውጫ/ ሾህ መቆንጠጫ እንኳን ቢሆን የብረት ዘር የተባለ ነገር ከቤቱም ሆነ ከኪሱ እንዳይኖር አጥብቀው መከሩት። በመላው ኢትዮጵያ ላይ እርቀ ሰላም እንደወረደ፣ የአጋንንት ሰራዊትና የአመጽ አርበኛ ሁሉ ከአገር እንደተሰደደና እንደተዋረደ በአዋጅ በከበሮ ተሰበከ። ከእንግዲህ ወዲህ አገራችን የምትመራው “በሰላም አርበኞች”/ “ለመሞት እንጂ ለመግደል” በማይታገሉ ከአመጽ ወኔ በነፁና በፀዱ የፖለቲካ መነኩሳት እንደሚሆን ተረጋገጠ።

ወያኔም ቢሆን ከእንግዲህ ወዲህ በሰላማዊ መንገድ ከተሸነፍሁ ስልጣኔን በሰላም እለቃለሁ ስላለ፣ ወያኔን በጠላትነት መፈረጅ ከከፍተኛ ስህተት የሚቆጠር ሆነ። እንዲያውም ወያኔ “ተባባሪያችን /አጋራችንና ወዳጃችን” ነው አሉ! የኢትዮጵያ ሕዝብ ወዳጅና ተቆርቋሪ መሆኑ ገሃድ ሆነ!!

መለኮታዊ ምስጢር ለመላዕክት ሰራዊት፣ ለሰላም አርበኞችና ለፖለቲካ መነኰሳት ተገለጠ። ለኖህ ከጥፋት ውሃ በኋላ "በማርያም መቀነት" (በቀስተ ደመና) ምልክት ስለመጭው ብሩህ ጊዜና ዘመን እንደተገለጸው ሁሉ!

የሰላም አርበኞች መዝሙርና የፖለቲካ መነኰሳት ትንቢት ከዳር እስከ ዳር ተሰማ። ተስተጋባ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ፀሎቱ የተሰማና የሰመረለት መስሎት ከአፉ የሚወጣው ቃል ሁሉ "ተመስገን፣ ተመስገን…"" ብቻ ሆነ! በተለይም ወያኔ በሰላማዊ መንገድ (በምርጫ ሳጥን) ከተሸነፍሁ ስልጣኔን የማልለቅበት ምን ምክንያት ይኖረኛል እያለ በተለያየ ስልትና ዘዴ "የተወዳዳሪ ያለህ"" /"የጠንካራ ተቃዋሚ" ያለህ እያለ መጣራት ጀመረ! ጠንካራ ተወዳዳሪና ተፎካካሪ (ተቃዋሚ) ቢኖረኝ ኖሮ ተወዳጅነቴንና ጠንካራነቴን ይበልጥ አድምቆ ያሳይልኝ/ ያረጋግጥልኝ ነበር። ካለማንም አሳሳቢነትና አስታዋሽነት/ በራሴ ፈቃድና ተነሳሽነት የጀመርኩትን የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ሂደት (democratization process) ያፋጥንልኝ ያቀላጥፍልኝ ነበር ብሎ በጐ ምኞቱንና ችግሩን ለባሕር ማዶ ጠባቂዎቹና ደጋፊዎቹ ጩኸቱን ማሰማት ቀጠለ።

በጡጫ የሚችለኝ እንደሌለ ዓለም ሁሉ ያውቅልኛል። አሁን የሚቀረኝና ማስመስከር የምፈልገው ኢትዮጵያ ውስጥ ጠንካራ ተወዳዳሪ አግኝቼ በዴሞክራሲያዊ ሩጫ ማንም ሊቀድመኝና ሊያልፈኝ እንደማይችል ነው። አይሆንም እንጂ ቢሆንማ መሸነፌም ከማሸነፌ ይበልጥ የሚያኰራኝና የሚያስደስተኝ ይሆን ነበር። የጀመርኩት የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ስር መስደዱንና ግብ መምታቱን ያረጋግጥልኝ ነበር!! አለ ወያኔ!! የወያኔን ትዕዛዝና ጉቦ ተቀብሎ "<u>ድጋፉን</u>" ለመግለጥ በብዙ ሺህ የሚቆጠር ሕዝብ (የወያኔ መንግሥት ሠራተኞች፣ ሰላዮች፣ ካድሬዎች፣ ሲቪል የለበሱ ወታደሮችና ፖሊሶች) አዲስ አበባ ከተማ ሰልፍ ወጣ። በማግስቱ ደግሞ ለወያኔ ስርዓት ያለውን የመረረና የከረረ ጥላቻ ለመግለጽ በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ ቁጥሩ ከሦስት ሚሊዮን የሚበልጥ ሕዝብ ተሰልፎ አደባባይ ወጣ። በብዙ የአገሪቷ ከተማዎች ተመሳሳይ ሕዝበ ትይንት ታየ። በሳምንቱ ሕልቆ መሳፍርት የሌለው ሕዝብ ድምጹን ለማስመዝገብ ተራውን ሲጠብቅ በየምርጫ ጣቢያው ከንጋት እስከ እኩለ ሌሊት ሐውልት ሆኖ ዋለ/ አደረ።

መሸነፉን ሲያውቅ፣ ወያኔ ገለልተኛ ታዛቢዎችንና የተቃዋሚ ፖለቲካ ተወካዮችን ከየምርጫ ጣቢያው አስፈራርቶና አስገድዶ አባረረ። የድምጽ ቆጠራውን ሂደት አደናቀፈ። አጨናገፈ። ቆጠራውን በራሱ ካድሬዎች፣ ተቀጣሪዎችና ሰላዮች ብቻ እንዲጠናቀቅ አዘዘ። በተሸነፈባቸው የምርጫ ጣቢያዎች ሁሉ ኮረጆ ገልብጦ /ራሱን መርጦ "አሸናፊነቱን" አወጀ። አድራጐቱን እየተከታተሉ ማስረጃ ይዘው የተቃወሙትን የቅንጅትና የሕብረት ዕጩዎችን አሰረ/ ገደለ።

ለሦስተኛ ጊዜ "አሸናፊነቱን" አስመሰከረ። ተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ወያኔ የፈጸማቸውን ጥፋቶችና ስህተቶች ለማረምና ለማስተካከል ያቀረቧቸው ዋና ዋና ክሶች ውድቅ ተደረጉ። ምክንያቱን ሁሉም ያውቀዋል። ፍርድ ቤቶችና የምርጫ ቦርድ የወያኔ ፓርቲ መዋቅር አካሎችና መሳሪያዎች ናቸው። ከዚህ ውጪ ለሚያስፈልግ ጉዳይ ደግሞ የስለላ፣ የፖሊስና የወታደር ኃይል አለ። እነርሱም እንደ ፍርድቤቶችና ምርጫ ቦርድ የወያኔ ፓርቲና መንግሥት ተላላኪዎችና ትዕዛዝ ፈጻሚዎች ናቸው።

ስለሆነም ወሳኙ ጥያቄ፣ ወያኔ በሦስተኛው የምርጫ ዙር ለምን ተሸነፈ? የሚለው አይደለም። ባለፉት ሁለት የምርጫ ዙሮችም ቢሆን ወያኔ ተወዳድሮ አላሸነፈምና። “ያሸነፈው” ዘንድሮ ኩልል ብሎ በታየው የውድድር ስልቱ ነው። ከተሜውንና ባላገሩን በየፈርጁ አስፈራርቶና አስገድዶ ርሱን እንዲመርጥ በማድረጉ ነው። ያፈነገጠውን ደግሞ በመግደል፣ በማሰር፣... ነው። ራሱን በራሱ ስለመረጠ ነው።

ታዲያ የዘንድሮውን የወያኔ ሽንፈት (“አሸናፊነት”) ካለፉት ሁለት ምርጫዎች ልዩ የሚያደርገው ምንድር ነው? የወያኔ አምባገነንነት ከምን ጊዜም ይበልጥ በዘንድሮው የምርጫ ሂደት ዕርቃኑን ወጥቶ ስለተጋለጠ ነው። የማስፈራሪያና የማስገደጃ መዋቅሩንና ኃይሉን በመጠቀም ለሦስተኛ ጊዜ ሕዝብ እንዲመርጠው ያስተላለፈው ትዕዛዝና ያደረገው መሰናዶ ስለከሸፈበት ነው።

በመጀመሪያው የምርጫ ዙር የታየው የተቃዋሚዎች ተሳትፎ ከቁጥር የማይገባ ስለነበር፣ ተወዳዳሪውና አሸናፊው ወያኔ ብቻ ነበር ብሎ ማለፍ ይቻላል/ ይቀላል። መጠነኛ በነበረው የሁለተኛው ዙር የተቃዋሚ ተሳትፎ የወያኔ ፍጹም አምባገነንነት ቦግ ብሎ መታየት ጀመረ። የወያኔ ዕጩዎችን አልመርጥ ያለውን፣ ከውድድር አልወጣ ብሎ የወያኔ ዕጩዎችን የተወዳደረውን፣ በምርጫ ሂደቱ ላይ የወያኔ ሕገወጥ ድርጊቶችን ያጋለጠውን ሁሉ ደበደበ፣ አሰረ፣ ገረፈ፣ ገደለ...። ይህም ሁሉ ሆኖ የአገርና የሕዝብ ችግር ከዓመት ዓመት (ለ14 ዓመት) ሲባባስና ሲቆለል እንጂ ሲቀረፍና ሲቀነስ አልታየም።

የሕዝብ ዕጣ ፈንታ በረሃብና በበሽታ መርገፍና ማለቅ ሆነ። ለወያኔ ስርዓት እንቅፋት መስሎ የታየ ሁሉ መታሰር/ መገደሉ፣ መሰደድ/ መኰብለሉ የማይቆም የማያባራ እየሆነ ቀጠለ። የመውጫና የማምለጫ ዕድል ያገኘ ሁሉ አገር ለቅቆ እየሸሸ ነው። አንዳንዶች ደግሞ በጾም በስለት ወደ አሜሪካ የመውጫ ሎተሪ በተስፋ ይጠባበቃሉ። በሌላ አነጋገር፣ እስከዛሬ በቆየው የወያኔ ዘመነ መንግሥት ከምን ጊዜም ይበልጥ ኢትዮጵያ ምርጫና ማምለጫ የሌለው ሰው ብቻ የሚኖርባት አገር ሆናለች። ለብዙሃኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ። ለዚህ ነው ወያኔ በዘንድሮው ዙር የኢትዮጵያን ሕዝብ እንደወትሮው በማታለል፣ በመደለል፣ በማስፈራራትና በማስገደድ ራሱን ሊመርጥ (ሊያስመርጥ) ያልቻለው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከወያኔ ስርዓት ተጨማሪና ቀጣይ ሞትና ጥፋት ብቻ እንጂ ከዚያ የተለየ የሚጠብቀው ነገር ስለሌለው ነው። መንግሥት የመሰየምና የመሻር መብት የኔ ከሆነ (የኔ ስለሆነ) ወያኔ ይውረድልኝ/ ይወገድልኝ ብሏል። ውሳኔውንና ድምጹን በምርጫ ካርድ አሰምቷል። ወያኔ ግን ዴሞክራሲ የመምረጥ መብት የሰጠሁህ የኔን መንግሥት እንድትመርጥና የጀመርሁትን የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ መቀጠል እንድችል ነው። የኔን መንግሥት ደግመህ ደጋግመህ የመምረጥና የማጽደቅ መብትህም እንደዚያው እንዲቀጥል ነው። በምናራምደው የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ምክንያት ከምዕራብ አገሮች የምትመጸወተው ዱቄት ተቋርጦ ሞተህ አልቀህ አገራችን ሰው አልባ እንዳትሆን ነው። ካለኔ ዴሞክራሲ የሚነጥቅህ እንጂ የሚሰጥህ ስለሌለ፣ ከኔ ሌላ ብትመርጥ ባርነትህንና ውርደትህን መልሰህ በራስህ ላይ ታነግሳለህ። ጠርተህ ተጣርተህ የነፍጠኞችንና የትምክተኞችን ዘመን ታመጣለህ/ ታድሳለህ።

የሰጠሁህ ዴሞክራሲ ሳያንስ ሳይቀነስ በየአምስት ዓመቱ ለኔው ለባለቤቱ መልሰህ የምስረክበውና መልሰህ የምትወስደው ነው! "ተቀብሎ የመስጠት/ ሰጥቶ የመቀበል" ትርጉምና ፍች ይሄ እና ይሄ ብቻ ነው። አራት ነጥብ! ስለሆነም፣ ወያኔን ባለመምረጥህ ሕጋዊና አስተዳደራዊ እርምጃ ተወስዶብሃል ይወሰድብሃልም። አለ ወያኔ። ለኢትዮጵያ ሕዝብ።

የፖለቲካ መብት ምንጭና ባለቤት እኔ ነኝ። ይህን መብት የሚሰጠኝም የሚነሳኝም ኃይል ሊኖር አይችልም። በጉልበት እነጥቅሃለሁ የሚል ካልሆነ በስተቀር። ይሄም ሆኖ ቢገኝ መልሱ <u>ሞቴ ወይም ነፃነቴ ነው</u>። ነገረው የኢትዮጵያ ሕዝብ። ለወያኔ።

<u>*ታዲያ ከእንግዲህ ወዲህ የኢትዮጵያ ሕዝብ የቀረው ያለው ምርጫ ምንድር ነው?*</u>

ከአሁን በኋላ የወያኔን አምባገነንነትና ሽብርተኝነት ማንሳትም ማውሳትም አስፈላጊ አይሆንም። ማንነቱና ምንነቱ ለአገር ለዓለም እንዲታይ ሜዳ ላይ ተሰጥቷል። ራሱ ወያኔ ማንነቱን በተግባር (በተግባሩ) መስክሯል። የኢትዮጵያን ሕዝብ የምርጫ ድምጽ ሰርቋል። መብቴ ይከበርልኝ ድምፄ ይታወቅልኝ ብሎ በሰላማዊ መንገድ አደባባይ የወጣውን ሕዝብ በያለበት በመደዳ ረሽኗል። ጨፍጭፏል።

በተወለዱበት፣ ባደጉበትም ሆነ በተገኙበት ከተማም ሆነ መንደር መብታቸውን ለመጠየቅ ለአቤቱታ የተሰባሰቡ ኢትዮጵያዊያን ሕይወታቸውን ተነጠቁ። የለየላቸው "ወንበዴዎች፣ ባንክ ዘራፊዎች፣ ቦዘኔዎች" ስለነበሩ ነው ከአንገት በላይ/ ግንባር ግንባራቸውን ብለን የሸረካከትናቸው/ ያፈራረስናቸው። አሉ የወያኔ ሹሞችና መሪዎች።

በሕገ መንግሥታችን መሠረት የተቋቋመውን የምርጫ ቦርድ መመሪያና ውሳኔ በመቃወማቸው ነው። በመሆኑም ሕገ መንግሥታችን ላይ በማመጻቸው ነው። በአጭሩ ሕገ ወጥ በመሆናቸው ነው። ሌላ ትርጉም የለውም ራሱ ሌላ ትርጉም ለመስጠት የሚደረግ ሙከራ ሁሉ ሕገ ወጥ ነው። አራት ነጥብ!

ስለዚህ የተወሰደባቸው እርምጃ ስነ ስርዓት፣ ሕግና ፀጥታ ለማስከበር መሆኑ ግልጽ ነው። የአሸባሪዎችንና የአመጽ ስልተኛ ፖለቲካ ድርጅቶችን ሴራ በእንጭጩ ለመቅጨት ነው። ሕዝቡ በአመጽ ተነሳስቶ የጀመርንለትን የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ሂደት በጅምርና በውጥን እንዳይቀጨው ነው። ሕዝቡ ራሱን በራሱ ጠልፍ በትምክህተኞችና በጉልተኞች ስርዓትና ወጥመድ ተመልሶ እንዳይወድቅ ነው። ማለትም አብዮታዊ ዴሞክራሲያችን ፈር እንዳይልቅ ነው። ለሕዝብና ለአገር ከአለን ፍጹም የሆነ ተቆርቋሪነት የመነጨ ነው! ብሎ አቅራራ። ወያኔ የወያኔ ወዳጅ ድርጅቶች በቅድሚያ የመሰከሩለት ይህንኑ ነው። እንደነርሱ አባባል ከሆነ እውነትም ወያኔ "ወዳጃችን (ወዳጃቸው) / አጋራችንና ተባባሪያችን" (አጋራቸው/ ተባባሪያቸው) ነው (ነበር) ማለት ነው!!

የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን የወያኔን ቃልና ቋንቋ የሚቀበለውና የሚተረጉመው በግልብጡ ነው። በሰላማዊ መንገድ ጠይቄአለሁ። ድምፄን ሰጥቻለሁ። ሂድልኝ ተወገድልኝ።

ምርጫዬን አክብርልኝ ነው። የምፈልገውን የምመርጠውና የምወስነው እኔ እንጂ አንተ አይደለህም። ነው የሚለው።

<u>*ታዲያ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከእንግዲህ ወዲህ የሚቀረው ምርጫ ምንድር ነው?*</u>

የኢትዮጵያ ሕዝብ ድምጹን እንደተሰረቀ የዓለም ሕዝብ ሁሉ አውቆታል። በዝርዝርና በማይካድ ማስረጃ አረጋግጦታል (ተረጋግጦለታል)። የወያኔ ደጋፊ መንግሥቶች እንኳን ሊክዱት ሊያስተባብሉት የማይችሉት ሆኖባቸዋል።

አገር ውስጥና ከአገር ውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የጀመሩትና የቀጠሉት ወያኔን የማጋለጥ ዘመቻ ፍሬውና ውጤቱ በማደግና በመጨመር ላይ ነው። በዚያው መጠን የወያኔ ዓለም አቀፍ ድጋፍ እያነሰ፣ እየተቀነሰና እየመነመነ በመሄድ ላይ ነው።

ይህም ሆና የወያኔን አምባገነንነትና ሕገ ወጥነት አውግዞ ስልጣኑን ለሕዝብ እንዲያስረክብ የጠየቀው መንግሥት እስካሁን አልታየም። በጥቅሉ የሚያስተላልፉት መልዕክት ተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶችና ወያኔ ተቀራርበውና ተቻችለው ችግራቸውን በሰላማዊ መንገድና በውይይት እንዲፈቱ ነው።

የወኔን "አሸናፊነት" ተቀብላችሁ፣ ያገኛችሁትን የምርጫ ድምጽ ለቃቅማችሁና አሰባስባችሁ የወያኔን ፓርላማ ተቀላቀሉ የሚለው የወያኔ ደጋፊ መንግሥቶች አሳብ ከኢትዮጵያ ሕዝብ አቋም ጋር ፍጹም የማይዋዋጥና የማይጣጣም ነው። ተቃዋሚዎች ይህን ሃሳብ መቀበል አለባቸው ማለት ከወያኔ ጋር ተስማምተው በአጋዚ ጦር የኢትዮጵያን ሕዝብ ማስፈጀት ይኖርባቸዋል ማለት ነው።

ያለ ሦስቱ ዋና ዋና የወቅቱ የፖለቲካ ተዋናዮች (ሕብረት፣ ቅንጅት፣ ወያኔ) ስምምነት አገሪትዋን ከገባችበት ከፍተኛ ቀውስና ውጥረት ለማውጣት ይከብዳል ከሚል ትክክለኛ መንደርደሪያ በመነሳት፣ <u>የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎት ሕብረት (ኢዴኃሕ) ያቀረበውን አማራጭ መፍትሔ (የብሔራዊ አንድነት መንግሥት = ጊዜያዊ የአደራ መንግሥት = (Government of national unity)</u> ወያኔ ሊቀበለው አልፈለገም። እስካሁን ድረስ። ይህንንም (ሁሉን አስታራቂ አማራጭ) ቢሆን እስካሁን የወያኔ ደጋፊ መንግሥቶች ገፍተው ሲደግፉት አልታዩም።

<u>*የውጭ መንግሥቶች ወያኔን የሚደግፉበትና የኢትዮጵያን ሕዝብ ፍላጎትና አቋም የሚቃወሙበት ምክንያት ምንድር ነው? በዴሞክራሲያዊ ስርዓትና በሕዝብ ነፃ ምርጫ የሚያምኑ ከሆኑ?*</u>

ኃያላንና የበለፀጉ መንግሥቶች፣ ኋላ ቀር በሆኑ በሦስተኛው ዓለም አገሮች የሚከተሉት ፖሊሲ የራሳቸውን ጥቅም የሚያስቀድም እንጂ የየሀገሩን ሕዝብ መብትና ፍላጎት የሚያስከብርና የሚያሳድግ አይደለም። ሆኖም ተደርጎም አያውቅም። በእያንዳንዳ የሦስተኛ ዓለም አገር የሚደግፉት መንግሥት፣ ሕዝቡን አፍኖም ሆነ ደልሎ በመቆጣጠር የደጋፊው መንግሥቶችን ጥቅም የሚጠብቅና የሚያስከብር መሆን አለበት (በኤኮኖሚ፣ በፖለቲካ፣ ሚሊቴሪ እስትራተጂ ወዘተ...)። ሕዝብ የተሟላ ዴሞክራሲና ነፃነት ካገኘ፣ ለራሱ ጥቅምና መብት የሚቆምለትንና የሚሟገትለትን ስርዓት እንጂ

ነፃነቱንና መብቱን ለሌላ አሳልፎ የሚሰጥበትን መንግሥት አይመርጥም። የውጭ መንግሥቶች ስራ አስፈጻሚና ተላላኪ ሊመኝም ሊፈልግም አይችልም።

ለዚህም ነው ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድ በኩል፣ ወያኔና ደጋፊው መንግሥቶች በሌላ በኩል ቆመው የተፋጠጡት። የኢትዮጵያ ሕዝብ ተባብርና ጠንክሮ በአቋሙ ጠንቶ ከቆየ፣ የትኛውም ዓይነት ኃይል ቢሆን አስገድዶ በቀጣይነት የጣለውንና የተፋውን መንግሥት እንዲቀበል ሊያደርገው አይችልም!

የውጭ መንግሥቶች ወያኔን የሚደግፉት ሕዝቡን አፍኖና አታልሎ ጥቅማቸውን ሊያስከብርላቸው እስከቻለ ድረስ ብቻ ነው። ከዚህ ውጭ የሆነ ተፈላጊነት የለውም። ስለዚህ የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች የኢትዮጵያን ሕዝብ አቋም ደግፈው መታገላቸውን ከቀጠሉ የወያኔ የውጭ መንግሥቶች ድጋፍ እየታጠፈ፣ እያጠረና እየተኰማተረ ይርቃል ያልቃል። የዛሬ የወያኔ ደጋፊ መንግሥቶች (በጠቅላላ አነጋገር) ነገ የተቃዋሚ ድርጅቶች ደጋፊ እንዲሆኑ ይገደዳሉ ማለት ነው።

ምናልባትም ይህንኑ በማስተዋልና በመደንገጥ ተቃዋሚዎቹ ያቀረቡለትን የብሔራዊ አንድነት መንግሥት አማራጭ (Government of National Unity) ወያኔ ተጨንቆ ወደሚቀበልበት ደረጃ ላይ ሊደርስም ይችል ይሆናል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ መብቱን ለማስከበር በሰላማዊ መንገድ ለሚያቀርበው ጥያቄ የሚያገኘው ተደጋጋሚ የአመጽ መልስ (የአጋዚ ኮማንዶ ጦር፣ ታንክና መትረየስ…) ከሆነ፣ አመጽና ሽብር ፈላጊው ራሱ ወያኔ መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው።

በዚህም ምክንያት ሕዝብን ከሰላማዊ ትግል ወደ ሙሉ አመጽ ምርጫ እንዲሄድ የሚያስገድደው እንደገና ራሱ ወያኔ መሆኑ ማንንም የማያከራክር ነው። ወያኔም አጥፍቶ ለመጥፋት ያለው ምኞት ከዚህ ሊዘል የማይችል ነው። እንደዚህ ከሆነ ደግሞ መጨረሻ ላይ የሚጠፋው ወያኔ ነው። በአሸናፊነትና በድል አድራጊነት መብቱን ጨብጦ የሚወጣው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው።